የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ
# FEDERAL NEGARIT GAZETA
## OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ስድስተኛ ዓመት ቁጥር ፪
አዲስ አበባ ጥቅምት ፲፩ ቀን ፲፱፻፺፪

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

6th Year No. 2
ADDIS ABABA - 22nd October, 1999

## ማውጫ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ፶፰/፲፱፻፺፪ ዓ.ም.
የኢትዮጵያ የእህል ንግድ ድርጅትን እንደገና ለማቋቋም የወጣ
የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ..................... ገጽ ፩ሺ፩፻፸፩

## CONTENTS

Council of Ministers Regulations No. 58/1999
Ethiopian Grain Trade Enterprise Re-establishment
Council of Ministers Regulations ............ Page 1171

### የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፶፰/፲፱፻፺፪
### የኢትዮጵያ የእህል ንግድ ድርጅትን
### እንደገና ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልሥንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፬/፲፱፻፹፯ አንቀጽ ፭ እና በመንግሥት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር ፳፭/፲፱፻፹፬ አንቀጽ ፵፯/፩/ (መ) መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል ።

፩· አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ "የኢትዮጵያ የእህል ንግድ ድርጅትን እንደገና ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፶፰/፲፱፻፺፪" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል ።

፪· እንደገና መቋቋም

፩· የኢትዮጵያ የእህል ንግድ ድርጅት /ከዚህ በኋላ "ድርጅቱ" እየተባለ የሚጠራው/ ከኢትዮጵያ የቅባት እህልና ጥራጥሬ ላኪ ኮርፖሬሽን ጋር ተዋህዶና የመንግሥት የልማት ድርጅት ሆኖ በዚህ ደንብ እንደገና ተቋቁሟል ።

፪· ድርጅቱ በመንግሥት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር ፳፭/፲፱፻፹፬ መሠረት ይተዳደራል ።

፫· ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን

በመንግሥት የሚሰየም አካል የድርጅቱ ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን ይሆናል ።

### COUNCIL OF MINISTERS REGULATIONS NO.58/1999.
### COUNCIL OF MINISTERS REGULATIONS TO PROVIDE FOR THE RE-ESTABLISHMENT OF THE ETHIOPIAN GRAIN TRADE ENTERPRISE

These Regulations are issued by the Council of Ministers Pursuant to Article 5 of the Definitions of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No. 4/1995 and Article 47/1/(d) of the Public Enterprises Proclamation No.25/1992.

1. *Short Title*

   These Regulations may be cited as the "Ethiopian Grain Trade Enterprise Re-establishment Council of Ministers Regulations No. 58/1999."

2. *Re-Establishment*

   1) The EThiopian Grain Trade Enterprise (hereinafter "the Enterprise") is hereby amalgamated with the Ethiopian Oil Seeds and Pulses Export Corporation and re-established as a public enterprise.
   2) The Enterprise shall be governed by the public Enterpirses Proclamation No. 25/1992.

3. *Supervising Authority*

   A body to be designated by the Government shall be the supervising authority of the Enterpirse.

፬· <u>ዋና መሥሪያ ቤት</u>

የድርጅቱ ዋና መሥሪያ ቤት አዲስ አበባ ሆኖ እንደ አስፈላጊነቱ በማንኛውም ሥፍራ ቅርንጫፍ ሊኖረው ይችላል ።

፭· <u>ዓላማ</u>

ድርጅቱ የተቋቋመባቸው ዓላማዎች የሚከተሉት ናቸው፤

፩· የእህል ምርቶችን ከአገር ውስጥ አምራቾች በመግዛት ለሀገር ውስጥና በዋነኛነት ለውጭ ገበያ ማቅረብ ፤

፪· የገበሬው የእህል ማምረት ፍላጐት እንዲያድግ አስተ ማማኝ ገበያ የሚያገኝበት ሁኔታ እንዲፈጠር እገዛ ማድረግ ፤

፫· ዓላማውን ከግብ ለማድረስ የሚረዱ ሌሎች ሥራዎችን መሥራት ፤

፮· <u>ካፒታል</u>

ለድርጅቱ የተፈቀደው ካፒታል ብር ፩፻፲፪ ሚሊዮን ፲፪ሺ ፬፻፶፬ (አንድ መቶ አሥራ ሁለት ሚሊዮን አሥራ ሁለት ሺ አራት መቶ ሃምሣ አራት ብር) ሲሆን ፤ ከዚህ ውስጥ ብር ፩፻፭ ሚሊዮን ፵፯ ሺህ ፸፱ (አንድ መቶ አምስት ሚሊዮን አርባ ሰባት ሺ ሰባ ዘጠኝ ብር) በጥሬ ገንዘብ እና በዓይነት ተከፍሏል።

፯· <u>ኃላፊነት</u>

ድርጅቱ ከአለው ጠቅላላ ንብረት በላይ በዕዳ ተጠያቂ አይሆንም ።

፰· <u>ድርጅቱ የሚቆይበት ጊዜ</u>

ድርጅቱ ላልተወሰነ ጊዜ ይቆያል ።

፱· <u>የተሻረ ደንብ</u>

የኢትዮጵያ የእህል ንግድ ድርጅት ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፩፻፬/፲፱፻፹፭ በዚህ ደንብ ተሽሯል ።

፲· <u>መብትና ግዴታን ስለማስተላለፍ</u>

በደንብ ቁጥር ፩፻፬/፲፱፻፹፭ ዓ.ም. ተቋቁሞ የነበረው የኢት ዮጵያ እህል ንግድ ድርጅትና የኢትዮጵያ የቅባት እህልና ጥራጥሬ ላኪ ኮርፖሬሽን በመባል ይታወቅ የነበረው ድርጅት መብቶችና ግዴታዎች በዚህ ደንብ ለድርጅቱ ተላልፈዋል ።

፲፩· <u>ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል ።

አዲስ አበባ ጥቅምት ፲፩ ቀን ፲፱፻፺፪ ዓ.ም.

መለስ ዜናዊ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

ጠቅላይ ሚኒስትር

4. *Head Office*

The Enterprise shall have its head office in Addis Ababa and may have branch offices elsewhere as may be necessary.

5. *Purposes*

The purposes for which the Enterpirse is established are:

1) to purchase grain from farmers and sell in local and mainly in export markets;
2) to contribute towards the stablization of markets for farmers' produces so that they will be encouraged to increase their outputs.
3) to engage in other related activities conducive to the attainment of its purposes.

6. *Capital*

The authorized capital of the Enterprise shall be Birr 112,012,454 (One hundred twelve million twelve thousand four hundred fifty four Birr) of which Birr 105,047,079 (One hundred five million fourty seven thousand seventy nine Birr) is paid up in cash and in kind.

7. *Liability*

The Enterprise shall not be liable beyond its total assets.

8. *Duration*

The Enterprise is established for an indefinite duration.

9. *Repeal*

The Ethiopian Grain Trade Enterprise Establishment Council of Ministers Regulations No.104/1992 is hereby repealed.

10. *Transfer of Rights and Obligations*

The rights and obligations of the Ethiopian Grain Trade Enterprise established under Regulations No. 104/1992 and the Enterprise known as the Ethiopian Oil Seeds & Pulses Export Corporation are hereby transferred to the Enterprise.

11. *Effective Date*

These regulations shall enter into force on the date of their publication in the Federal Negarit Gazeta.

Done at Addis Ababa, this 22nd day of October, 1999.

MELES ZENAWI

PRIME MINISTER OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ
BERHANENA SELAM PRINTING ENTERPRISE